የአፍሪካ ፕሮግራም
ቻታም ሃውስ

# የተጓደለ ምርጫ የኢትዮጵያን ለውጥ አይታደግም

## በአህመድ ሶሊማን



***ኢትዮጵያ ወደ ምርጫ እየተቃረበች ባለችበት በአሁኑ ወቅት በሃገሪቱ ሃጥ እየተንሰራፋ የሄደው የጸጥታ መደፍረስ፣ ሰብአዊ ቀውስና የትግራዩ ደም አፋሳሽ አስከፊ ግጭት ለሀጋሪቱ ዘርፈ ብዙ ቅራኔዎች የፖለቲካ መፍትሄ በአስቸኳይ እንደሚያስፈልግ ከመቼውም በላይ ግልጽ አድርጎታል፡፡***

ኢትዮጵያ በመጪው ሰኔ 14 ሃገር አቀፍ ምርጫ ታካሂዳለች፡፡ የፌደራሉ መንግስት የምርጫው ውጤት በቀጣይ ሊፈጽማቸው ላቀዳቸው ታላላቅ ክንውኖች ማለትም አዲስ ህገ መንግስት ማርቀቅና ምናልባትም በክልሎች መሃከል ያሉ ድንበሮችን ለመለወጥ/ለማሻሻል ጨምሮ ሌሎች እቅዶቹን ለመተግበር የሚረዳው የህዝብ ይሁንታ እንደሚያቀዳጀው የሚያምን ይመስላል፡፡

ምርጫው በዶ/ር አብይ አህመድ ለሚመራውና በ2011 አ.ም ከቀድሞው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) አባልና አጋር ፓርቲዎች ለተመሰረተው የብልጽግና ፓርቲ እውነተኛ ፈተና ሆኖ ተቀምጧል፡፡ በመጀመሪያ ለነሃሴ 2012 አ.ም የተቀጠረው የኢትዮጵያ ሃገራዊ ምርጫ- አንዴ በኮሮና ቫይረስ ስርጭት ሌላ ጊዜ ደግሞ በጸጥታ ምክንያት - ለሁለት ያህል ጊዜ ተራዝሟል፡፡

ምንም እንኳን የመጀመሪያው ዙር ምርጫ በመጪው ሰኞ ሰኔ 14 ቀን 2013 ኢ.ም እንዲካሄድ ቢታቀድም በብዙ የሃገሪቱ አካባቢዎች እየተባባሰ የሚገኘው የጸጥታ መደፍረስ፣ እየከፋ የሚገኘው ሰብአዊ ቀውስና ከገዢው ፓርቲ ጋር ከፍተኛ ፉክክር ያደርጋሉ ተብለው ይጠበቁ የነበሩ ፓርቲዎች ከወዲሁ ራሳቸውን ማግለላቸው ጋር ተዳምሮ ለብዙ ጉዳዩን በአንክሮ ለሚከታተሉ ሰዎች ምርጫው የሃገሪቱን ቁስል ከማከም ይልቅ ችግሮቿን እንዳያባብሰው እያሰጋቸው ይገኛል፡፡

***አስቸጋሪ ተግዳሮቶች***

ቀጣዩ ሃገር አቀፍ ምርጫ ኢትዮጵያ የመድብለ ፓርቲ ምርጫን ከጀመረችበት ባለፉት 30 አመታት ውስጥ ስድስተኛው ሲሆን ያለፉት ምርጫዎች በጉልህ የሚታዩ ችግሮች የተስተዋሉባቸው ሆነው አልፈዋል፡፡ በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት በምርጫ 2007 ወደ ስልጣን ከመጣውና 100 ፐርሰንት የምክር ቤት መቀመጫ ከተቆናጠጠው እንዲሁም ባለፉት 6 አመታት በተለይ በብዙ የፖለቲካ ነውጥና ወጀብ ውስጥ ካለፈው የኢህአዴግ መር መንግስት የወጣ ነው፡፡

ምርጫውን ተከትሎ የተከሰተው ጸረ መንግስት ተቃውሞ በኢህዴግ ውስጥ የአመራር ለውጥን ያስከተለ ሲሆን ጠ/ሚ አብይ አህመድ ከ ሶስት አመት በፊት ወደ መሪነቱ መንበር እንዲመጡ ገፊ ምክንያት በመሆን አገልግሏል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመጀመሪያ ወራት የስልጣን ቆይታቸው አሌ የማይባሉ መሰረታዊ ለውጦችን ያመጡ ሲሆን በሃገሪቱ ውስጥ ብሄራዊ አንድነትና ዴሞክራሲን ለማምጣት ቃል ገብተው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህም ጥረታቸው ከኤርትራ ጋር የተፈጠረውን አንጻራዊ ሰላም ጋር ተዳብሎ ከሁለት አመት በፊት የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ እንዲሆኑ አብቅቷቸዋል፡፡

ነገር ግን ባለፉት ጥቂት አመታት በተለይ ደግሞ ከትግራዩ ግጭት ወዲህ በኢትዮጵያ የተከሰተው ዘርፈ ብዙ ቀውስና እርሱን ተከትሎ የተቀጣጠለው የሽምቅ ትግል ከፍተኛ ውድመትና እልቂት በዜጎችና በንብረት ላይ አስከትሏል፡፡ የሰብአዊ ቀውሱና የመብት ጥሰቱ ተባብሶ የቀጠለ ሲሆን ከ 1.7 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ከቀያቸው ሲፈናቀሉ ከ 5 ሚሊዮን የሚልቁቱ በአስቸኳይ የምግብ እጥረት እንደተጠቁና ረሃብ በዜጎች ላይ እያንዣበበ እንደሚገኝ አለም አቀፉ የመንግስታቱ ድርጅት አስታውቋል፡፡

በአሜሪካ የሚመራው አለም አቀፍ ማህበረሰብ ግጭቱንና ሰብአዊ ቀውሱን ተከትሎ በአቸኳይ እልባት እንዲያገኝ ሲያሳስብ የቆየ ሲሆን ማሳሰቢያው ይሄ ነው የሚባል ፋይዳ ባለማበርከቱ በቅርቡ በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግስታት ላይ የጉዞና የእርዳታ ማእቀብ ያስተላለፈ ሲሆን ግጭቱ አሁንም የማይቆም ከሆነና የረድኤት አቅርቦቶችን ማደናቀፍ ከቀጠለና ሰብአዊ ቀውሱ ተባብሶ ከሄደ ተጨማሪ ማእቀቦችን ለመጣል እንደሚገደድ አስታውቋል፡፡ ጉዳዩ የፖለቲካ መፍትሄ በአስቸኳይ እንዲያገኝም ወትውቷል፡፡

በተቃራኒው የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩን በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት አድርጎ የቆጠረው ሲሆን አጋር መንግስታት ከፌደራል መንግስቱ ጋር ተባብረውና ተከባብረው መስራት እንዳለባቸው ሲያሳስብ ይደመጣል፡፡ ነገር ግን የኤፌዴሪ መንግስት መረዳት የሚገባው ነገር ግጭቱ እየቆየ በሄደ ቁጥር የግጭቱ ውል እየተወሳሰበ እንደሚሄድ ነው፡፡ ለዚህም የኤርትራን ሰራዊት ከትግራይ የማስወጣት ጉዳይ በአስቸኳይ መከናወን የሚኖርበት ነገር ሲሆን ለዚህም አስፈላጊውን ዝግጅት ቶሎ ማጠናቀቅ ተገቢ ይሆናል፡፡

**የተጓደለና የተዛነፈ ምርጫ**

መጪው ምርጫ ትግራይን ጨምሮ የጸጥታ መደፍረስ ባጋጠማቸው አካባቢዎች ማለትም በአንዳንድ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ምእራብ ኦሮሚያና ደቡብ ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ አካባቢዎች በሰኔ 14 የማይከናወን ይሆናል፡፡ በሶማሌና በሃረሪ ክልሎች ምርጫው ከምርጫ ወረቀት ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ሙሉ ለሙሉ ወደ ጳጉሜ የተዛወረ ሲሆን በአጠቃላይ በ 102 የፌደራል ምክር ቤት ወንበሮች (ከ547 አጠቃላይ) ላይ በቀጣዩ ሳምንት ምርጫ የማይካሄድ ሲሆን ይሄም ወደ 18 ፐርሰንት የፌደራል ምክር ቤት ወንበሮችን ይሸፍናል፡፡

የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በአቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥም ሆኖ የተቋም ግንባታ ላይ እየተሳተፈ እንደሚገኝ ይናገራል፡፡ ይሁን እንጂ በምርጫው ሂደት ውስጥ የተስተዋሉ እጥረቶች ከፍተኛ እንደነበሩ ለመታዘብ የጉዳዩ ልሂቅ መሆንን አይጠይቅም፡፡ የመራጮች ምዝገባ፣ የምርጫ ቁሳቁሶችን ማሟላትና ምርጫ አስፈጻሚዎችን መመልመል ከፍተኛ መዝረክረኮች ተስተውሎባቸዋል፡፡ምርጫው በክረምት መግቢያና መውጫ ወቅት እንደመካሄዱ መጠን በትራንስፖርትና በመገናኛ ዘዴዎች ላይ የሚፈጥረው ጫና በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡ የኢፌዴሪ መከላከያ ሰራዊት የምርጫ ቁሳቁሶችን ማንቀሳቀስና የምርጫውን ጸጥታ የመጠበቅ ሃላፊነት የተሰጠው ቢሆንም በትግራይ ባለው ጦርነት ምክንያት በሚፈለገው መጠን ማገልገል እንደተሳነው የአደባባይ ሃቅ ነው፡፡ በተጨማሪም ከሩብ ሚሊዮን የሚልቅ ቁጥር ያለው የምርጫ አስፈጻሚና አስተባባሪን የመመልመል፣ የማሰልጠንና የማሰማራት ሃላፊነት በብሄራዊው ምርጫ ቦርድ በኩል ከፍተኛ ተጽእኖ ፈጥሯል፡፡

ወጣም ወረደ መጪውና በሁለት ጊዜ የሚደረገው ብሄራዊ ምርጫ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም በአሁኑ ሰአት በእጅጉ አስፈላጊ የሆነውን አገር አቀፍ ውይይትና ስክነትን ከማምጣት ይልቅ፣ በምርጫ ውጤት ላይ የተመሰረተ አላስፈላጊ ንትርክን፣ ምርጫ ወለድ ግጭትንና ተጨማሪ በመንግስትና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠር መካረርን ሊያስከትል እንደሚችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡

**ግዙፍ ችግሮች ነገር ግን ጥቂት መሻሻሎች**

የፌደራል መንግስቱና የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ መጪው ምርጫ ካለፉት ምርጫዎች ሁሉ ጋር ሲነጻጸር ነጻ፣ አሳታፊና በውድድር የተሞላ እንደሚሆን ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ በምርጫው ወደ 37 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ወደ 46 ለተገመቱ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችና ጥቂት የግል ተወዳዳሪዎች ድምጽ ይሰጣሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የፌደራሉ ምክር ቤት 547 መቀመጫ ያለው ሲሆን ዜጎች የክልል ምክር ቤት አባላትን ለመሰየምና በደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ አዳዲስ ክልሎችን ለማዋቀር በሚደረግ ህዝበ ውሳኔ ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ የኢፌዴሪ ህገመንግስት አሸናፊ ተደርጎ የሚሰየመው ፓርቲ/ፓርቲዎች ከግማሽ የሚልቅ የምክርቤት ወንበሮችን ማሸነፍ እንደሚጠበቅበት/እንደሚጠበቅባቸው ሲደነግግ፣ በዚህም መሰረት ገዢው ብልጽግና ፓርቲ ከየትኛውም ተፎካካሪ ይልቅ ወደ 2800 የሚጠጉ የፌደራልና የክልል ምክር ቤት ተወዳዳሪዎችን በማቅረብ ምርጫውን ለማሸነፍ ይታትራል፡፡ የገዢው ፓርቲ ተፎካካሪዎች አነስተኛ ተወዳዳሪዎችን ከማቅረባቸው በተጨማሪ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ብቻ መታጠራቸው ለብልጽግና እንደ እድል ከመቆጠሩ በተጨማሪ የእርስ በእርስ ፉክክራቸው ለተቃዋሚዎች የሚሰጠውን ድምጽ ስለሚያሳሳ ብልጽግና ፓርቲ ከወዲሁ አብላጫ የምክር ቤቶች መቀመጫዎችን በቀላሉ መቆጣጠር እንደሚችል እንዲገመት ገፊ ምክንያት ሆኗል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ እንደተጠቀሰው ብልጽግና ፓርቲ ምርጫውን እንደሚያሸንፍ ከወዲሁ ቢገመትም በተወሰኑ አካባቢዎች ከፍተኛ ፉክክር እንደሚገጥመው ይጠበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ /ኢዜማ/ እና ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ በተለይ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከተሞች ከፍተኛ ውድድር እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል፡፡ የአማራ ብሄራዊ ንቅናቄ /አብን/ በአማራ ክልል ከአማራ ብልጽግና ፓርቲ ጋር የሚያደርገው ፉክክር ከወዲሁ እየተጠበቀ ነው፡፡ የአፋር ህዝብ ፓርቲና የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር በአፋርና ሶማሌ ክልል ውስጥ ከገዢው ብልጽግና ፓርቲ ጋር ከፍተኛ ውድድር ሊያሳዩ እንደሚችሉ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

በተቃራኒው በኦሮሚያ ክልል ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ ተፎካካሪ ይሆናሉ ተብለው ይጠበቁ የነበሩት የኦሮሞ ፌደራላዊ ኮንግረስና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከወዲሁ ራሳቸውን ከምርጫው ራሳቸውን ማግለላቸው ለብልጽግና ፓርቲ 178 አካባቢ የሚሆነውን የፌደራል ምክርቤት መቀመጫ ያለምንም ጠንካራ ፉክክር በቀላሉ እንዲቀዳጅ እድል ከፍቶለታል፡፡ ይህም በአሁኑ ወቅት ትልቁ ጥያቄ ገዢው ፓርቲ ኦሮሚያ ውስጥ ያሸንፋል ወይስ አያሸንፍም ሳይሆን በክልሉ የሚገኘው ማህበረሰብ የሚፈልገውን ፓርቲ በነጻነት መምረጥ አለመቻሉ የሚፈጥረው ቅሬታና መከፋት በክልሉና በሃገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ሊፈጥረው የሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ እስከምን ድረስ ይዘልቃል የሚለው ጥያቄ ይሆናል፡፡

**የፖለቲካ መፍትሄ ለነገ የሚባል መሆን የለበትም**

በገዢው ብልጽግና ፓርቲ ውስጥ ያለው ተስፋ በምርጫው የሚገኘው ስልጣን መንግስት ላቀዳቸው ለውጦች በተለይም ሃገር አቀፍ የማህበረሰብ ውይይትና ፖለቲካዊ ውይይት መድረኮችን ከመፍጠር አኳያ አይነተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ነው፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ሃገሪቱ የተጋረጡባት አስቸጋሪ ተግዳሮቶች የፖለቲካ መፍትሄ ብቻ የሚፈታቸው እንደሆኑ መረዳት በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሃገሪቱን የሚንጧት ርእዮተ አለማዊ ቅራኔዎች መፍትሄ የሚያገኙት በእውነተኛ ድርድርና መግባባት እንጂ ብዙ ችግሮች በታጀሉበት ምርጫ እንዳልሆነ መረዳት በእጅጉ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የቅርብ ጊዜ ክስተቶች እንደሚያሳዩት መንግስት በምርጫው ማግስት ሊተገብራቸው ያቀዳቸው ውይይቶች ሁሉን አሳታፊ የመሆናቸው ጉዳይ በብዙ ሰዎች ዘንድ በጥርጣሬ ሲታይ ይታያል፡፡ በተለይም በቅርብ የፌደራሉ ምክር ቤት በሽብርተኝነት የፈረጃቸው የኦሮሚያና የትግራይ ክልል የፖለቲካ ቡድኖች በውይይቱ የመሳተፋቸው ጉዳይ ያበቃለት ይመስላል፡፡ በድጋሚ መሰመር ያለበት ጉዳይ የገዢው ፓርቲ ምርጫውን በከፍተኛ ድምጽ ማሸነፍ ጉዳይ በሃገሪቱ ስር እየሰደደ ለመጣው የሰላም እጦትም ሆነ የመዋቅራዊ ችግሮችና የርእዮተ አለም ቅራኔ ይሄ ነው የሚባል ፋይዳ ሊያበረክት እንደማይችል መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

ምርጫውን ተከትሎ ሊፈጠር የሚችለው ተጨማሪ መካረርና ቅራኔ የሃገሪቱን የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ከማሳደሩ በተጨማሪ ዘላቂ ሰላምን ከሚያስገኝ የፍኖተ ካርታ ውይይትና ገለልተኛና ነጻ ተቋሞችን ለመገንባት ለሚደረገው ጥረት ጋሬጣ ይሆናል። በተጨማሪም እየከፋ ከመጣው ውስጣዊና ውጫዊ ጫና አኳያ ምርጫው በህዝቦች መሃከል የተፈጠረውን ስንጥቃት ለመሙላትም ሆነ ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ የሚመጣውን ጫና ከመቀነስ አንጻር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ለብዙዎች ጥያቄ ፈጥሮ ይገኛል። ከዚህም አንጻር ጠ/ሚ አብይ አህመድ በአስቸኳይ ግጭቶችን ማስቆምና እውነተኛ ድርድር ከተፎካካሪዎቻቸው ጋር የመጀመር ታሪካዊ ሃላፊነት በጫንቃቸው ይገኛል።